**ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ አካባቢ ድጋፎች መርሃግብር**

< በሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ መረጃን ለማግኘት እና ስለ ሌሎች የድጋፍ ዕድሎች ይመዝገቡ>

**ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ ምንድ ነው?**
የሲያትል ፓርት በ2019 የሳውዝ ኪንግ ካውንት ፈንድ በ2019 ያቋቋመ ሲሆን በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አጋርነት ለማሳደግ እና በአየር ማረፊያ አከባቢ የሚገኙ በታሪክ በሚገባ እንክብካቤ ያልተደረገላቸው ማህበረሰቦች ድጋፎችን ያደርጋል። ፈንዱ ከ2019 እስከ 2023 ባለው ጊዜ $10 ሚሊዮን መድቦ በብሄርና በባህል ስብጥር በሆነው አካባቢ የድምጽ ብክለት ለመቀነስ፤ የአካበቢ ጤና ና ዘለቄታነት መልስ ለመስጠት ይሰራል። የፈንዱ አንደኛ ምዕራፍ በኢኮኖሚያዊ ማገገም ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን በኦገስት 2020 ተጀምሯል።

**የአካባቢ ድጋፍ**
የSKCF **በ**Burien, Des Moines, Federal Way, Normandy Park, SeaTac, እና Tukwila የሚከናወን በአየር ማረፊያ አጠገብ ያሉ ማህበረሰቦች አከባቢን ለማሳደግ የሚያግዝ ፕሮጀክት አዲስ ምዕራፍ ነው። ማህበረሰብ-መር ቡድኖች እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ በሚከተሉት ተግባራት የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ጥያቄ እንዲያቀርቡ ተጋብዘዋል:

- የህዝብ ቦታዎች ማሻሻያዎች (ፓርኮች፣ የትምህርት መጫወቻ ሜዳዎች፣ የህዝብ አደባባይ ወይም የፖርት መኖርያ ጣብያ)
- የመሳሪያዎች  ወይም የዕደጥበብ ስራ ተገጣሚዎች
- ወይም የጎረቤት ወይም አከባቢ ተንካባካቢ ፕሮጀክቶች።

SKCF  መርኃግብር ስኬታማ አየር ማረፊያማህበረሰብ ኢኮሎጂ (ACE) ወደ ተጨማሪ በሲያትል ታኮማ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት (SEA) አከባቢ ያሉት ማህበሰረብ ይበለት ተደራሽ ያደርጋል። በሳውዝ ኪንግ ካውንቲ የሚገኙ ማህበረሰቦች ፍትሃዊ ባልሆነ የመሬት አጠቃቀም እና የኢኮኖሚ መፈናቀል ምክንያት አለአግባብ የአካባቢ ጉዳት ደርሶባቸው በቀጣይነት ወደ ደቡብ ተገፍተዋል። ከ COVID-19 ባስከተለው ተጨማሪ የጤናና የኢኮኖሚ ጉዳት በሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ከሌላ የካውንቲው አከባቢ ይልቅ ነዋሪዎች አነስተኛ ፓርክና እና የአረንጓዴ ስፍራ ያላቸው በመሆኑ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት አስፈላጊ ሆኗል።

**መኸር 2020: የመጀመርያው የ SKCF የአካባቢ ድጋፎች መርሃግብር ምዕራፍ**
ፖርቱ አሁን የመጀመርያው የሳወዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ አካባቢ ድጋፎች ምዕራፍ የእቅድ ሃሳብ (ፕሮፖዛል) በመቀበል ላይ ነው። ፕሮፖዛል እስከ ዲሰምበር 4 2020 12 ፒኤም መቅረብ አለባቸው። የሚሰጠው ድጋፍ እስከ $20,000 ሲሆን በ3:1 ተዛማጅነት(ከታች ዝርዝሮችን)ይመልከቱ መሆን አለበት።

**ስለ ፈንዱ መረጃዎች**

- በዚህ ምዕራፍ $435,000 ፈንድ ተዘጋጅቷል።
- እስከ $20,000 መጠየቅ ይቻላል
- ፕሮጀክቶች በህዝብ ሃብት ላይ መሆን አለባቸዉ።

ፕሮጀክቶቹ በ3:1 መዛመድ አለባቸው ማለት በፖርቱ የሚሰጠው ዶላር ከድጋፍ ተቀባይ ወይም ድጋፍ አጋሮች በሶስት ዶላር የፕሮጀክቱ ዋጋ መዛመድ አለበት። ፖርቱ ይህንን ለማዛመድ የበጎ ፈቃድ ጊዜ፣ የህዝብ በዓላት ተሳታፊዎች፣ የሰዓት ስምምነት፣ የተተከሉ ዛፎች ዕድሜ፣ የካርበን ቅነሳ፣ በዓይነት የተደረጉ ድጋፎች፣ የፕሮጀክት አጋሮች ድጋፍ እና ገንዘብ ጨምሮ የተለያዩ አገባቦችን ይጠቀማል።

- ፕሮፖዛሉን የሚያቀርቡ በ501(c)3 ወይ 501(c)6 መሰረት ለትርፍ ያልተቋቋሙ ወይም በ501(c)3 ፊስካል ስፖንሰር የሚሠራ የማህበሰረብ ቡድን መሆን አለባቸው።
- ድርጅቱ በኤርፖርት አካበቢ በሚገኙ ማህበረሶቦች የኢኮኖሚ እና አካባቢ ፍትህ ማጣት ላይ የሰራበትን ልምድ ማቅረብ አለበት።
- ድርጅቶቹ ፕሮፖዛላቸውን በጽሁፍ ማቅረብና ከአጥኚ ፓናል ጋር በሚካሄደዉ ውይይት ላይ መሳተፍ አለባቸው።

**እንዴት ማመልከት ይቻላል**

- በ SKCF የአካባቢ ድጋፎች መርሃግብር ለመዝገብ የሚያስፈልጉ ሁሉም ነገሮች 'Documents' በሚል በ_ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ጥያቄችን ለመጠየቅና መረጃዎችን ለማግኘት በVendorConnect እንደ Plan Holder መመዝገብ አለብዎት። ወደ ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ ጥያቄ ገጽ በመሄድ መመዝገብ ይቻላል። (ስለምዝገባ ዝረዝር መመሪያዎችን ለማግኘት VendorConnect External User Guide ሚለውን ያንብቡ። ጥያቄን ለመጠየቅ Ask Question"የሚለውን በተን ይንኩ።

**የማስገቢያ ዝርዝሮች እና ቀነ ገደብ**

- ሁሉም ሰነዶች ወደ e-submittals-sa@portseattle.org. ኢሜይል መደረግ አለባቸው
- የእቅድ ሃሳብ ለማቅረብ ቀነ ገደቡ እስከ ዲሰምበር 4 2020 12 ፒኤም ነው።

**የመረጃ መድረኮች**

ስለ ፕሮፖዛል ሂደት ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት የቨርችዋል መድረኮቹ በአንዱ ላይ ይሳተፉ። በመረጃ መድረኮቹ አመልካቾች VendorConnect ለመጠቀም ቴክኒካል ድጋፍ ማግኘት ወይም ፕሮፖዛሉ እና የማስረከብ ሂደቱን በተመለከተ ጥያቄን ለመጠየቅ ይችላሉ። **እርስዎ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት የቋንቋ ትርጉም ይቀርባል።** እባክዎ ከታች ያለው ሊንክ በመጠቀም RSVP ያድርጉ።( RSVP በ VendorConnect ላይ አይጠቀሙ።)
https://www.portseattle.org/programs/south-king-county-fund-environmental-grants-program.

**ቀደም ሲል በACE ፈንድ የተደረጉ ፕሮጀክቶች አብነት**

**ሚድወይ ፓርክ እና የመጫወቻ ቦታ ጥበቃ(Midway Park & Play Area Restoration)** – ደስ ሞኒስ ሮተሪ ፋውንዴሽንDes Moines Rotary Foundation, ደስ ሞኒስ- ድጋፉ ወጣቶች እና ቤተሰቦች የሚዝናኑበት ፓርክ ውበትንና የማዝናናት ደረጃውን ከፍ ለማድረግ የሚያስችል ስራ በጎ ፈቃድተኞች ፓርክ ጥገና እንዲካሂዱ ያስቻለ ነው።

**ፉርምቦት(Farmbot)** – ኢኮቴክ(Ecotech) በከተማ ጋርደን፣ ቁልፍ ቴክኖሎጂ ላባራቶሪ ዶስ ሞኒስ- ይህ ፕሮጀክት STEM(ሳይንስ ቴክኖሎጂ፣እንጅነሪንግ እና ሂሳብ) እንዲሁም ጤናማ የምግብ ትምህርትን ያጣመረ ሲሆን በደስ ሞኒስ ፓስፊክ ሪጅ አካባቢ ያለው ከፍተኛ ድህነት ያለበት አካባቢ የማህበረሰብ ጋርደን የሚያገለግል ሮቦት አሰራር ለወጣቶች ማስተማርን የሚሰራ ነው።

**ኒው ፊዩቸርስ ፉርም(New Futures Farm)** – ሳውዝ ዌስት ወጣቶችና ቤተሰብ(Southwest Youth and Family Services)፣ ቡሪየን እና ሲታክ- ይህ ፕሮጀክት በቡሪየን እና ሲታክ አከባቢ ያሉ ቤተሰቦችን አነስተኛ ገቢ ባላቸው አካባቢዎች የማህበረሰብ ጋርደን እንዴት ማልማትና መጠበቅ እንደሚቻል በማስተማር ቤተሰቦች ጤናማ የምግብ ትምህርት ይሰጣል።

**ሲታክ ኢትኒክ ማህበረሰብ ኢኮሎጂ ግንኙነቶች(SeaTac Ethnic Community Ecology Connections)** –ፓርትነር በስራ( Partner in Employment)ሲታክ- ድጋፉ በሲታክ ከሚገኙ ስደተኞች በባህል ላይ ጠቃሚ ተሳትፎ በማድረግ ስደተኛ ማህበረሰቦች በአካባቢ ትምህርት፣ በማደረጃት እና በማህበረሰብ የጽዳት ተግባራት ማነሳሳት እንዲሁም በአከባቢ ስራዎች በቀጣይነት ለመተግበር የአነስተኛ ቢዝነሶች መጨመርን ተሳቢ ያደረገ ነው።

የፕሮጀክት ሙሉ ዝርዝር ይመልከቱ

**ጥያቄዎች?**

- ጥያቄ ለመጠየቅ በVendorConnect ይግቡ ወይም በስብሰባ ለመሳተፍ። ሁሉም የሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ ዕቅድ ባለቤት ጥያቄዎች መልሶች በ VendorConnect ላይ ይለጠፋሉ። ለመመዝገብ ድጋፍ ለማግኘት VendorConnect External User Guide ይመልከቱ ወይም ቴክሊካል ድጋፍ ለማግኘት በስብሰባ ላይ መገኘት ይችላሉ።
- ስለ መስፈርቶቹ ተጨማሪ ገለጻ ለማግኘት የ FAQs መመልከት ይችላሉ

**ዲስክላይመር**

ዲስክላይመር: ይህ የፖርቱ ይፋዊ የሚገኝበት ድረ ገጽ አይደለም። ይፋዊ RFP መረጃ እና ይበልጥ አዲስ መስፈርቶች በፖርቱ VendorConnect system ይገኛሉ።